# ታላቅ የሰላማዊ ሠልፍ ጥሪ

## የ25 ዓመት አረመኔያዊ የወያኔ አገዛዝ እንዲያበቃ የተጠራ ታላቅ ሠላማዊ ሰልፍ በለንደን!

በአማራ በኦሮሞና በሌሎች አካባቢወች የተቀጣጠለው ሥር-ነቀል ሕዝባዊ አመፅን ለማፈን በንፁህን ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ላይ የትግራይ ወያኔ አጋዚ ወታደሮችየኢትዮጵያንወጣቶችጨፍጭፈዋል።

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችም በከፍተኛ ድብደባ ቆስለውና ተሠባብረው ባልታወቁ እስር ቤቶች ታጉረዋል። ይኸ አልበቃ ያለው የትግራይ ወያኔ ቡድን፣ መላው የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርስ በዘርና በቋንቋ በመከፋፈል፣ ሕዝቡን ለማጫረስ ያጠመደውን ወጥመድ የኦሮሞና የአማራ ልጆች እጅ ለጅ ተያይዘው በጣጥሰው በመጣል ይኸን አስከፊ ሥርዓት ፈንቅሎ ለመጣል ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ አቅርበዋል።

እኛም በለንደን የምንገኝ ኢትዮጵያውያን፣ የወገኖቻችን ሞት ሞታችን መሆኑን፣ ድላቸው ድላችን መሆኑን ተገንዝበን፣ የትግል አጋርነታችንን ለመግለፅ ከጎናቸው የተሰልፍን መሆናችንን ለማረጋገጥ፤ብሎም የታላቋ ብሪታኒያ መንግሥት የተቻለውን ሁሉ ጫና እንዲያሳድር በጠቅላይ ሚንስትርዋ መሥርያ ቤት (office) ከፍተኛ የተቃውሞ ሰልፍ እናደርጋለን።

ስለዚህ፣ በብሪታኒያ አገር የምትገኙ ኢትዮጵያንውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ ሰኞ አገስት 15 ቀን 2016 ዓ.ም (15 August 2016) በትራፋልጋር እስኰዌር (Trafalgar Square) ከቀኑ ) 01:00 pm ጀምሮ እንድትገኙ ጥሪአችንን እናስተላልፋለን።

**በብሪታኒያ የኢትዮጵያውያን ህብረት ለፍትህ**

**ኢትዮጵያ ለዘልዓለም በክብር ትኑር!**

**ለተጨማሪ መረጃ፤** የስልክ ቁጥር ፤ 07903448667 ኢሜል፡ eujb.london@gmail.com